1ኛ ዓመት ልዩ እትም
1st Year Special Issue

ሐረር ነሐሴ [illegible] ቀን 1987
HARAR Sept 11/1995

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ
# HARAR NEGARI GAZETA

HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| ያንዱ ዋጋ 5.00 | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |

ማውጫ

ሕግ ቁጥር ልዩ እትም
የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት አዋጅ ገጽ 1

## የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት በሥራ ላይ መዋሉን ለማሳወቅ የወጣ አዋጅ

የሐረሪ ሕዝብ ክልል ም/ቤት አባላት ጳጉሜ 6/1987 የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥትን ያጸደቁ በመሆኑ የሚከተለው ታውጇል።

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ሕገ-መንግሥቱ በሥራ ላይ ስለመዋሉ

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት ጳጉሜ6/87 ጀምሮ ሙሉ በሙሉ በሥራ ላይ ውሏል።

3. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጳጉሜ 6/87 ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ሐረር

ጳጉሜ 6/87

አብዱላሂ ኢድሪስ ኢብራሂም

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዚዳንት

## መግቢያ

እኛ የሐረሪ ህዝብ ክልል ምክር ቤት አባላት የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ለዘመናት ሲደርስባቸው የነበረውን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ብሔራዊ ባህላዊና ኃይማኖታዊ ጭቆና፣ ጫናና ተጽዕኖ በተለያየ ስልት መልክና ቦታ ሲታገሉ ቆይተው በመጨረሻ በግንቦት ወር 1983 ለዚህ ሁሉ ምክንያት የሆነውን ሥርዓት በማያዳግም ሁኔታ ለመጣል በመቻሉ በተለይ ጭቁን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር ታሪካቸው፣ ባህላቸውና ቋንቋቸውን ለማዳበር በአጠቃላይ ብሔራዊ ህልውናቸውን ለመጠበቅ የሚያስችላቸውን ምቹ ሁኔታ መፈጠሩንና ይህም ህዳር 29 ቀን 1987 በኢትዮጵያ ህዝቦች በጸደቀው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት መረጋገጡን በመገንዘብ፣ [illegible]

የሐረሪ ሕዝብ ምንም እንኳ በምዕተ ዓመታት ለሚቆጠር ዘመን ራሱን በራሱ ያስተዳድር በራሱ ታሪክ ወግና ባህል ይኮራ የነበረ ቢሆንም ከአንድ መቶ ዓመት በፊት በተደረገበት ወረራ በነፍጠኛው ሥርዓት ሥር ከመውደቁም በላይ ይህንን ስርዓት ለማስወገድ በተለያዩ ጊዜያት ባደረገው ንቅናቄና ትግል ምክንያት ለግርፋት፣ ለእስራት ብሎም ለስደት በመዳረጉ በራሱ ክልል በቁጥር አናሳ ከመሆኑ የተነሳ የእወካከል ስልት ማስፈለጉን በመረዳት፣

የሐረሪ ሕዝብ ሲደርስበት የነበረውን ግፍና ጭቆና ሲካፈሉት ከነበሩት ህዝቦች መካከል የአካባቢው የኦሮሞ ህዝብ ጋር በመሆን የነፍጠኛውን ሥርዓት ከእነሳሱ ጀምሮ በጋራ ሲታገሉና ሲዋጉ የነበሩ በመሆናቸውና አሁንም ለዚህ ድል የበቁት በጋራ በመሆኑ የክልሉን አስተዳደር ከሌሎች የክልሉ ነዋሪ ህዝብ ጋር በመሆን በጋራ ማቋቋምና መምራት ያለባቸው መሆኑን በማጤን፣

መጪው ዘመን በሐረሪ ህዝብ አወቃቀር ዋንኛ ተጠቃሚ የሆኑት የሐረሪ ህዝብና የኦሮሞ ህዝብ የተገኙትን ብሔራዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለማረጋገጥ ክልሉንና የክልሉን ህዝብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ማፋጠን ያለባቸው መሆኑን በመረዳት፣

የመረጠንን ህዝብ በመወከል በፌደራል ሀገ-መንግሥቱ መሠረት ይህንን የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ ሀገ-መንግሥት ዛሬ ጳጉሜ6,1987 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ አጽድቀናል።

## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች
### አንቀጽ 1
### የክልሉ መንግሥት ስያሜ

ይህ ሀገ-መንግሥት ብሔራዊ ክልላዊ የመንግሥት አወቃቀር ይደነግጋል። በዚህ ሀገ-መንግሥት የሚዋቀረው መንግሥት "የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት" በሚል ስም ይጠራል።

### አንቀጽ 2
### የወሰን ክልል

የሐረሪ ህዝብ ክልል በሰሜን በኮምቦልቻና በጀርሶ ወረዳዎች በምስራቅ በጉርሱምና በባቢሌ ወረዳዎች በደቡብ በፈዲስ ወረዳና በምዕራብ በአለማያ ወረዳ የሚያዋስን ነው።

### አንቀጽ 3
### የሐረሪ ሕዝብ ክልል ሰንደቅ ዓለማና አርማ

1. የሐረሪ ህዝብ ክልል ሰንደቅ ዓላማ መደቡ ነጭ ሆኖ ከላይኛው ጠርዝ ገባ ብሎ ወደ አግድም የሚዘልቅ ቀይ መስመር ይኖረዋል። እንዲሁም ከታችኛው ጠርዝ ወደ አግድም የሚዘልቅ አረንጓዴ መሥመር ይኖረዋል።
2. የሰንደቅ አላማው ቀለማት የሚያስተላልፉት መልዕክት፣

ሀ.ነጩ መደብ የክልሉ ህዝብ በፍትህና በእኩልነት ላይ ለተመሠረተ ሰላም ያለውን ስሜትና ፍላጎት ያመለክታል፣

ለ. ቀዩ መሥመር ህዝቡ ለመብቱና ለነፃነቱ ያደረገውን ትግልና የከፈለውን መስዋዕትነት ያመለክታል፤

ሐ. አረንጓዴው መስመር ህዝቡ ለልማትና ለዕድገት ቆርጦ መነሳቱንና የወደፊቱን ብሩህ ተስፋ ያመለክታል።

3. የሐረሪ ህዝብ ክልል ዓርማ ይኖረዋል፣ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 4
## ርዕሰ ከተማ

የሐረሪ ህዝብ ክልል ርዕሰ ከተማ ሐረር ነው።

## አንቀጽ 5
## የሥራ ቋንቋ

የሐረሪ ህዝብ የሥራ ቋንቋ ሐረሪና ኦሮምኛ ናቸው።

## አንቀጽ 6
## የህገ-መንግሥት ገበላይነት

ይህ ህገ-መንግሥት የሐረሪ ሕዝብ ክልል የበላይ ሕግ ነው። ማንኛውም የክልሉ ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያና፣ ውሣኔ ከዚህ ሕገ-መንግሥት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## አንቀጽ 7
## የፆታ አገላለጽ

በዚህ ህገ-መንግሥት ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል።

# ምዕራፍ ሁለት
# መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች

ማንኛውም የሐረሪ ህዝብ ክልል የሥልጣን አካላት በዚህ ምዕራፍ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የማክበር ግዴታ አለባቸው።

## ክፍል አንድ
## ሰብዓዊ መብቶች
## አንቀጽ 8
## የእኩልነት መብት

ዜጎች ሁሉ በህግ ፊት እኩል ናቸው፤ በመካከላቸው ምንም አይነት ልዩነት ሳይደረግ በህግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል። በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር ብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በኃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ በማንኛውም አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ዜጎች ሁሉ እኩልነት ተጨባጭ የህግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው።

## አንቀጽ 9
## የኃይማኖት የእምነትና የአመለካከት ነፃነት

1. ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የህሊናና የኃይማኖት ነፃነት አለው። ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ኃይማኖት ወይም እምነት የመያዝ ወይም የመቀበል እና ኃይማኖቱን ወይም እምነቱን በግልም ሆነ ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣ ወይም የማስተማር መብትን ያካትታል።

2 ወላጆችና ህጋዊሞግዚቶች በእምነታቸው መሠረት የኃይማኖታቸውንና የመልካም ሥነ ምግባር ትምህርት ለመስጠት ልጆቻቸውን የማሳደግ መብት አላቸው።

3 ኃይማኖትና እምነት የመግለጽ መብት ሊገደብ የሚችለው የህዝብን ደህንነት፣ ሰላምን፣ ትምህርትን፣ የህዝቡን የሞራል ሁኔታ፣ የሌሎች ዜጎች መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶችን ለማረጋገጥ በሚወጡ ህጎች ብቻ ይሆናል።

## አንቀጽ 10

## የግል ህይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት

1. ማንኛውም ሰው የግል ህይወቱ፣ እና ግላዊነቱ የመከበር መብት አለው። ይህ መብት ከህግ ውጭ መኖሪያ ቤቱን ሰውነቱን ከመመር መር እንዲሁም በግል ይዞታው ሥር ያለው ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን ያካትታል።

2. ማንኛውም ሰው በግል የሚፈጽማቸውና የሚጻጻፋቸው፣ በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎች፣ እንዲሁም በቴሌፎን፣ በቴሌኮሙንኬሽንና በኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች የማይደፈሩ ናቸው።

## አንቀጽ 11

## የነፃነት መብት

1. ማንኛውም ሰው በህግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ነፃነቱን አያጣም

2 በህግ ከተደነገገው ውጭ ማንኛውም ሰው ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም።

3. ማንኛውም የተያዘ ሰው በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አለው።

## አንቀጽ 12

## የመዘዋወርና የመሥራት ነፃነት

ማንኛውም ሰው በዚህ ክልል ውስጥ የመንቀሳቀስና በሕግ ያልተከለከለ ማንኛውንም ሥራ ሰርቶ የመኖር ነፃነት አለው።

## አንቀጽ 13

## ከኢሰብአዊ አያያዝ የመጠበቅ መብት

1. ማንኛውም ሰው ኢሰብአዊ ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብአዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው።

## ክፍል ሁለት

## ዴሞክራሲያዊ መብቶች

## አንቀጽ 14

## ሀሳብን የመግለጽ፣ የመደራጀት፣ የመሰብሰብና

## ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብት

1. ማንኛውም ሰው ሃሳቡን በቃል፣ በጽሁፍ ወይም በህትመት፣ በሥነ ጥበብ መልክ ያለማንም ጣልቃ ገብነት በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ የመግለጽና የማሰራጨት መብት አለው።

2. ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማህበር የመደራጀት መብት አለው። ሆኖም ሕግ በመጣስ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በሕገ-ወጥ መንገድ ለማፍረስ የሚሠራ ድርጅት የተከለከለ ነው።

3. ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን ጦር መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብት አለው። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 15
## የጋብቻና ቤተሰብ የመመስረት መብት

1. በህግ በተወሰነው የጋብቻ እድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በራሳቸው ሙሉ ፍቃደኝነት ጋብቻ የመፈፀምና ቤተሰብ የመመስረት መብት አላቸው።

2. በህግ የተደነገጉ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም በባህል በኃይማኖት ሥነ-ሥርዓት የተፈፀመ ጋብቻ ዕውቅና አግኝቶአል።

## አንቀጽ 16
## የንብረት መብት

1. ማንኛውም ሰው ንብረት የማፍራትና የመያዝ መብቱ የተጠበቀ ነው ።

2. የሀገሪቱ ህግ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግሥት የክልሉን ውሱን የመሬት ስፋት ግንዛቤ ውስጥ የሚያስገባ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ ያወጣል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/ የተደነገገ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ ይችላል።

## አንቀጽ 17
## የመምረጥና የመመረጥ መብት

በሕግ የተደነገጉ መስፈርቶችን የሚያሟላ ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ በማንኛውም ደረጃ በክልሉ በሚካሄድ ምርጫ የመምረጥና የመመረጥ መብቶች አሉት።

## አንቀጽ 18
## ብሔራዊ መብት

የሌሎች ብሔሮችና ብሔረሰቦች አባላት ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች መከበር እንደተጠበቀ ሆኖ የሐረሪ ሕዝብ ክልል የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ መብት የሚከበርበት ክልል ነው። ሆኖም የኦሮሞ ሕዝብ ባህል ታሪክና ቋንቋ እንዲዳብር እንዲያድግና በሥራ ላይ እንዲውል እንዲሁም የክልሉ ኦሮሞ ሕዝብ በአስተዳደሩ እንዲካፈል ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል።

## አንቀጽ 19
## የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የህዝቦች መብት

በፌደራሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 35 የተደነገገው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሐረሪ ህዝብ ክልል የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ያለው መብት የተጠበቀ ነው።

## አንቀጽ 20
## ስለ ሠራተኞች፣ ስለ ሴቶች፣ ስለ ህፃናትና ስለሌሎች መብቶች

በፌዴራሉ ህገ-መንግሥት ስለ ሠራተኞች፣ ስለሴቶች፣ ስለህፃናትና ስለ አካባቢ ደህንነት መብቶች እና ሌሎች

የተደነገጉ መብቶች ሁሉ በዚህ ህገ-መንግሥት ተፈፃሚነት አላቸው።

## ምዕራፍ ሦስት

## የክልሉ መንግሥት አወቃቀር

### አንቀጽ 21

### የመስተዳድር እርከን

ለአስተዳደር ሥራ በሚያመች መልኩ የክልሉ መስተዳድር በሁለት እርከን ይዋቀራል። እንዲሁም በቀበሌ የተከፋፈለ የአስተዳደር አካላት ይኖሩታል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

### አንቀጽ 22

### የክልሉ መንግሥት የሥልጣን አካላት

የሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግሥት የህግ አውጪ፣ የህግ አስፈፃሚና የዳኝነት ሥልጣን አካላት ይኖሩታል።

## ምዕራፍ አራት

## የሐረሪ ሕዝብ ክልል ምክር ቤት አወቃቀርና አወካከል

### አንቀጽ 23

### የሐረሪ ሕዝብ ክልል ምክር ቤት

1. የሐረሪ ሕዝብ ክልል ምክር ቤት በፌዴራል ህገ-መንግሥት ለክልሎች የተሰጠውን ሥልጣን ተግባራዊ የሚያደርግ የክልሉ ከፍተኛ የፖለቲካና፣ የሕግ አውጪነት ሥልጣን ያለው አካል ነው።
2. የሐረሪ ሕዝብ ክልል ምክር ቤት ከሐረሪ ብሔራዊ ጉባዔ 14 አባላት እንዲሁም ከህዝብ ተወካዮች ጉባዔ 22 አባላት በአጠቃላይ 36አባላት ያሉት ምክር ቤት ነው።

### አንቀጽ 24

### የምክር ቤቱ ጉባዔዎች

1 የሐረሪ ሕዝብ ክልል ምክር ቤት ሁለት ጉባዔዎች ይኖሩታል። እነሱም፣

ሀ/ የህዝብ ተወካዮች ጉባዔና

ለ/ የሐረሪ ብሔራዊ ጉባዔ ናቸው።

2. የህዝብ ተወካዮች ጉባኤ በዚህ ህገ-መንግሥት አንቀጽ25/1 እንደተመለከተው የሚወከሉ ሃያ ሁለት አባላት ይኖሩታል።

3 የሐረሪ ብሔራዊ ጉባዔ በዚህ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 25/2 እንደተመለከተው የሚወከሉ አሥራ አራት የሐረሪ ብሔረሰብ አባላት ይኖሩታል።

### አንቀጽ25

### የጉባዔዎች አከፋፈል፣ አወካከልና አመራረጥ

1 የህዝብ ተወካዮች ጉባዔ አባላት በሁለት የምርጫ ክልሎች የሚወከሉ አባላት ያሉት ጉባዔ ነው። አወካከሉ፦

ሀ/ ከጁገል ምርጫ ክልል አራት አባላት እና

ለ/ ከጁገል ውጪ ካሉት የከተማ ቀበሌዎችና የገበሬ ቀበሌ ማህበራትን የሚያጠቃልል የምርጫ ክልል አስራ ስምንት አባላት፣ ይመረጣል።

2 የሐረሪ ብሔራዊ ጉባዔ አባላት በክልሉ ውስጥና ከክልሉ ውጭ በሌላ የኢትዮጵያ ክልሎችና ከተሞች ከሚኖሩ የሐረሪ ብሔረሰብ አባላት ይመረጣል።

2. ማንኛውም ሰው ለማንኛውም አላማ በማህበር የመደራጀት መብት አለው። ሆኖም ሕግ በመጣስ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በሕገ-ወጥ መንገድ ለማፍረስ የሚመሠረት ድርጅት የተከለከለ ነው።

3. ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን ጦር መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብት አለው። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 15

## የጋብቻና ቤተሰብ የመመስረት መብት

በህግ በተወሰነው የጋብቻ እድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በራሳቸው ሙሉ ፍቃደኝነት ጋብቻ የመፈፀምና ቤተሰብ የመመስረት መብት አላቸው።

2. በህግ የተደነገጉ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም በባህል በኃይማኖት ሥነ-ሥርዓት የተፈፀመ ጋብቻ ዕውቅና አግኝቶአል።

## አንቀጽ 16

## የንብረት መብት

1. ማንኛውም ሰው ንብረት የማፍራትና የመያዝ መብቱ የተጠበቀ ነው ።

2. የሀገሪቱ ህግ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግሥት የክልሉን ውሳኔ የመሬት ስፋት ግንዛቤ ውስጥ የሚያስገባ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ ያወጣል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/1/ የተደነገገ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ ይችላል።

## አንቀጽ 17

## የመምረጥና የመመረጥ መብት

በሕግ የተደነገጉ መስፈርቶችን፣ የሚያሟላ ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ በማንኛውም ደረጃ በክልሉ በሚካሄድ ጸጥ ምርጫ የመምረጥና የመመረጥ መብቶች አሉት።

## አንቀጽ 18

## ብሔራዊ መብት

የሌሎች ብሔሮችና ብሔረሰቦች አባላት ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች መከበር እንደተጠበቀ ሆኖ የሐረሪ ሕዝብ ክልል የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ መብት የሚከበርበት ክልል ነው። ሆኖም የኦሮሞ ሕዝብ ባህል ታሪክና ቋንቋ እንዲዳብር እንዲያድግና በሥራ ላይ እንዲውል እንዲሁም የክልሉ ኦሮሞ ሕዝብ በአስተዳደሩ እንዲካፈል ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል።

## አንቀጽ 19

## የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የህዝቦች መብት

በፌዴራሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 39 የተደነገገው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሐረሪ ህዝብ ክልል የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ያለው መብት የተጠበቀ ነው።

## አንቀጽ 20

## ስለ ሠራተኞች፣ ስለ ሴቶች፣ ስለ ህፃናትና ስለሌሎች መብቶች

በፌዴራሉ ህገ-መንግሥት ስለ ሠራተኞች፣ ስለሴቶች፣ ስለህፃናትና ስለ አካባቢ ደህንነት መብቶች እና ሌሎች

3. የጉባዔው አባላት ምርጫ ነፃና፣ ቀጥተኛ፣ በሆነ ድምጽ በምስጥር በሚሰጥበት ሥርዓት ይፈጸማል።

## ምዕራፍ አምስት

## የሐረሪ ህዝብ ክልል ምክር ቤት እና የጉባዔዎቹ

## ሥልጣንና ተግባር

## ክፍል አንድ

## አንቀጽ 26

## የሐረሪ ህዝብ ክልል ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የሐረሪ ህዝብ ክልል ምክር ቤት የህዝብ ተወካዮች ጉባዔ እና የሐረሪ ብሔራዊ ጉባዔ በጋራ የሚሰበሰቡበት ምክር ቤት ነው። ይህ ምክር ቤት የክልሉ ከፍተኛ የስልጣን አካል ሲሆን ተጠሪነቱም ለክልሉ ህዝብ ነው።

2. የሐረሪ ህዝብ ክልል ምክር ቤት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ/ የክልሉን ሕገ-መንግሥት እና ሌሎች ሕጎችን ያወጣል፤

ለ/ በዚህ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ41 በተደነገገው መሠረት የክልሉን ሕገ-መንግሥት ያሻሽላል፤

ሐ/በፌዴራል ሕገ-መንግሥት ለክልሎች የተሰጠውን ሥልጣን በክልሉ ተግባራዊ ያደርጋል።

መ/ ለክልሉ ፕሬዚደንትነት በሐረሪ ብሔራዊ ጉባዔ ጠቋሚነት የሚቀርበውን ዕጩ በ $^{2}/_{3}$ ድምጽ መርምሮ ይመርጣል፤

ሠ/ የክልሉን የውስጥ አስተዳደር ያዋቅራል ያደራጃል፤

ረ/ የክልሉን የህዝብ ደህንነትና ፀጥታን በሚመለከት ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ያወጣል፤

ሰ/ ለሕዝብ ተወካዮች ጉባዔና በክልሉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚቀርቡለትን ረቂቅ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ፖሊሲ ዎች መርምሮ ያጸድቃል፤

ሸ/ በክልሉ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚቀርቡትን የቢሮ ኃላፊዎችና ተመሳሳይ ሥልጣን ያላቸውን ኃላፊዎች ሹመት ያፀድቃል፤

ቀ/ በክልሉ ፕሬዚደንት የሚቀርቡትን የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንትና ም/ፕሬዚደንት ጠቅላይ ዐቃቢ ሕግ የኦዲትና ቁጥጥር ዋና ኃላፊዎች እና የፖሊስ ኮሚሽነሩን ሹመት ያፀድቃል፤

በ/ በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የሚቀርቡትን ዳኞች ሹመት ያፀድቃል፤

ተ/ በሁለቱ ጉባዔዎች የሚቀርቡትን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ሹመት ያፀድ ቃል፤

ቸ/የክልሉን የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ፣ ደንብና መመሪያ ያወጣል፤

ነ/ ለክልሉ በተሰጠው የገቢ ምንጭ ወሰን ግብርና ታክስ ይጥላል፤

ኘ/የክልሉን ዓመታዊ በጀት ያፀድቃል፤

## አንቀጽ 27

## የምክር ቤቱ አባላት መብትና ግዴታ

1 ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል በምክር ቤቱ በሚሰጠው ድምጽ ወይም እስተያየት ምክንያት አይከሰሰም፤ አስተዳደራዊ እርም ጃም አይወሰድበትም።

2 ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለ ም/ቤቱ ፍቃድ አይያዝም በወንጀልም አይከሰስም፤

3 ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል የመረጠው ህዝብ እመኔታ ባጣበት ጊዜ ከምክር ቤት አባልነት ይወገዳል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

## ክፍል ሁለት

## የጉባዔዎች ሥልጣንና ተግባር

## አንቀጽ 28

## የህዝብ ተወካዮች ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር

የሕዝብ ተወካዮች ጉባዔ በክልሉ ምክር ቤት ከሚኖረው ስልጣንና ተግባር በተጨማሪ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. ማንኛውም የኢኮኖሚ ልማትና የማኅበራዊ ልማት ፖሊሲ ስትራቴጂን በተመለከተ ረቂቅ ሕግ ያመነጫል፤ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስጸድቃል።

2. የግብርና ታክስ አዋጆችን ያመነጫል፤ በክልሉ ምክር ቤት በማቅረብ ያፀድቃል።

3 የክልሉን በጀት ገምግሞ ለክልሉ ምክር ቤት ያቀርባል።

4 ከክልሉ የምክር ቤት አባላት መካከል ለክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልነት አራት አባላትን ይጠቁማል።

5 የጉባዔውን ስብሰባ የሚመሩ አፈ ጉባዔ፤ ምክትል አፈ ጉባዔና ፀሐፊ ጉባዔ የሚይዝ በራሱ ከመካከሉ ይመርጣል።

## አንቀጽ 29

## የሐረሪ ብሔራዊ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር

የሐረሪ ብሔራዊ ጉባዔ በክልሉ ምክር ቤት የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

1 የሐረሪን ብሔረሰብ ቋንቋና ባህል በሚመለከት ፖሊሲና ሕግ ያወጣል።

2. በክልሉ ውስጥ የሐረሪን ብሔረሰብ ታሪክና ባህል የሚያንፀባርቁ ቅርሶ ቅርፆች፤ የመቃብር ቦታዎች የመስጊድ የአድባራት አጠባበቅ በሚመለከት መመሪያ ያወጣል።

3. የሐረሪ ብሔረሰብ በፌዴራል መንግሥት የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሚወክል (የሚወክሉ) አባል ወይም አባላትን ይመርጣል።

4. ለክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል የሚሆኑ ከክልሉ ምክር ቤት አባላት መካከል ሦስት አባላትን ይጠቁማል።

5. የክልሉን ፕሬዚዳንት ይጠቁማል።

6. የጉባኤውን ስብሰባ የሚመሩ አፈ ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ ቃለ-ጉባኤ የሚይዝ በኋላ ከመካከሉ ይመርጣል።

## አንቀጽ 30

## የጉባዔዎቹ የምክር ቤቱ ስብሰባ፣ ውሳኔና የሥራ ዘመን

1. ሁለቱ ጉባኤዎች በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖራቸዋል።

2. የሐረሪ ህዝብ ምክር ቤት በ3ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል። ሆኖም የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ወይም ከእያንዳንዱ ጉባዔ 1/3ኛው ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አስቸኳይ ስብሰባ ያደርጋል።

3. የጉባዔዎቹና የክልሉ ምክር ቤት ስብሰባ ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይኖራል።

4. በጉባዔዎቹና በክልሉ ምክር ቤት ማንኛውም ውሳኔ የሚተላለፈው በዚህ ህገ-መንግሥት በተለይ ካልተደነገገ በስተቀር በስብሰባው በተገኙ አባላት በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍ ነው።

5. የምክር ቤቱና የጉባዔዎቹ የሥራ ዘመን የፌዴራል ምክር ቤቶች የሥራ ዘመን ነው።

6. የክልሉ ምክር ቤትና ጉባዔዎቹ ስለአሰራ ራቸው የሚሰቸው የሆኑ ደንቦችን ያወጣሉ።

## ምዕራፍ ሰድስት

## የሐረሪ ሕዝብ ክልል የሕግ አስፈፃሚ አካል

## አንቀጽ 31

## የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አካል

የሐረሪ ሕዝብ ክልል የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የክልሉ ከፍተኛ የሕግ አስፈፃሚ አካል ነው።

## አንቀጽ 32

## የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት

1. የሐረሪ ሕዝብ ክልል የሥራ አስፈፃሚው ኮሚቴ ሰባት አባላት ይኖሩታል።

2. ከሰባቱ አባላት ፕሬዚዳንቱ፣ ምክትል ፕሬዚዳንቱና በሐፊው በዚህ ሕገ-መንግሥት የተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባር ሲኖራቸው፣ የቀሩት አራት አባላት በፕሬዚዳንቱ አቅራቢነት ምክር ቤቱ የሚሰጣቸውን ተግባራት ያከናውናሉ።

3. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ይሆናል።

## አንቀጽ 33

## የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር

የሐረሪ ሕዝብ ክልል የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. በኢትዮጵያ ፌዴራል መንግሥት፣ በክልሉ ምክር ቤትና በሐረሪ ብሔራዊ ጉባዔ የወጡ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤

2. የክልሉ የመስተዳድር አካላትንና ሥራን ይመራል፤ ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤

3. የክልሉ ማኅበራዊ ዕድገትና ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማፋጠን የሚያስችሉ እቅዶችና ፕሮግራሞች ያዘጋጃል፤ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

4. የመስተዳድሩን በጀት በማዘጋጀት ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

5. የክልሉን ቢሮዎችና የሥራ ዘርፎች ያስተባብራል፤ ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤

6. ሕግና ሥርዓት በክልሉ መከበሩን ያረጋግጣል፤

7. ከሌሎች የፌዴራል መንግሥት አባላት ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፤ ይደራደራል፤ ስምምነት ይፈራረማል፤

8. የክልሉን ምክር ቤት ስብሰባ ይጠራል፤

9. የልማትና የማኅበራዊ ጉዳይ ፀጥታና ደህንነትን በሚመለከት የሕግና የፖሊሲ ረቂቆችን ለክልሉ ምክር ቤት ያቀርባል፤

10. በክልሉ ምክር ቤት በሚሠጠው ሥልጣን መሠረት ደንቦችንና መመሪያዎችን ያወጣል፤

11. ስለ ሥራው እንቅስቃሴ ለክልሉ ምክር ቤት ሪፖርት ያቀርባል።

## አንቀጽ 34

## የክልሉ ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር

የሐረሪ ሕዝብ ክልል ፕሬዚዳንት የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. የክልሉን መስተዳድር በበላይነት ይመራል፤

2. የክልሉ ምክር ቤትና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔዎችን ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ያረጋግጣል፤

3. የክልሉን መስተዳድር በመወከል ከፌዴራል መንግሥት ወይም ከፌዴራሉ መንግሥት አካላት ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤

4. የክልሉን ምክር ቤት ስብሰባ ይጠራል፤ ይመራል፤ ያስተባብራል፤

5. የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ም/ፕሬዚዳንት እንዲሁም ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግና የፖሊስ ኮሚሽነሩን ለምክር ቤቱ በማቅረብ ያሾማል፤

6. በክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሣኔ መሠረት የመስተዳድሩ የተለያዩ አካላት ኃላፊዎችን በምክር ቤቱ ያሾማል፤ ያሽራል፤ ከሥራ ያግዳል፤ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፤

7. የክልሉን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እንዲሁም የመስተዳድሩ የተለያዩ አካላትን ሥራ በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤

8. የክልሉ ደህንነትና ፀጥታ መከበሩን ያረጋግጣል፤ የክልሉን ፖሊስ ኃይል በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤
9. ፕሬዚዳንቱ በዚህ አንቀጽ ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ከፊሉን በውክልና ለምክትል ፕሬዚዳንቱ ሊሰጥ ይችላል፤
10. ለክልሉ ምክር ቤትና ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል።

## አንቀጽ 35
## የክልሉ ምክትል ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር

የክልሉ ምክትል ፕሬዚዳንት የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

1. የክልሉ ም/ፕሬዚዳንት ፕሬዚዳንቱ በሌሉበት ፕሬዚዳንቱን ተክቶ ይሠራል፤
2. በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና በፕሬዚዳንቱ የሚሰጠውን ሥራ ያከናውናል፤

## አንቀጽ 36
## የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ፀሐፊ ሥልጣንና ተግባር

የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ፀሐፊ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

1. የክልሉ ምክር ቤትና ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል፤
2. የምክር ቤቱንና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን ጽ/ቤት ያደራጃል፤ ጽ/ቤቱን በኃላፊነት ይመራል፤
3. በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እና በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

## ምዕራፍ ሰባት
## የዳኝነት ሥልጣንና አካላት

## አንቀጽ 37
## የዳኝነት ሥልጣን

1. በሐረሪ ሕዝብ ክልል የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው፤
2. በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማንኛውም የመንግሥት አካል፣ ከማንኛውም ሌላ ተፅዕኖ ነፃ ነው፤
3. ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነፃነት ያከናውናሉ፤ ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም።

## አንቀጽ 38
## የዳኝነት አካላት

1. በፌዴራሉ ሕገ-መንግሥት በዚህ ጉዳይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድቤት በክልሉ ጉዳዮች ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል።
2. የሐረሪ ሕዝብ ክልል አንድ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ አንድ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና እንደ አስፈላጊነቱ የሚቋቋሙ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ይኖሩታል፤
3. በክልሉ የሚገኙ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በዚህ ሕገ-መንግሥት እውቅና አግኝተዋል። በመሆኑም በተሻለና በተቀላጠፈ መልኩ የሚሠሩበት ሁኔታ ይመቻቻል፤

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የክልሉ የዳኝነት አካላትን በጀት ለክልሉ ምክር ቤት በማቅረብ ያስወስናል፤ ሲፈቀድም በጀቱን ያስተዳድራል።

## አንቀጽ 39
## የዳኝነት አሿሿም

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት በክልሉ ፕሬዚዳንት አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ፤
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞችና የክልሉ ፍርድ ቤት ዳኞች በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ። የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የዳኞችን ሹመት ለክልሉምክር ቤት ከማቅረቡ በፊት የፌዴራሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በእጩዎቹ ላይ ያለውን አስተያየት መጠየቅና አስተያየቱን ከራሱ አስተያየት ጋር በማያያዝ ለክልሉ ምክር ቤት የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፤
3. የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኞችና የሸሪዓ ፍርድ ቤት ዳኞች በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ፤
4. በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ ዳኞች የዲሲፕሊንና የዝውውር ጉዳይ በሚመለከተው የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ይወሰናል።

## ምዕራፍ ስምንት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች
## አንቀጽ 40
## የፌዴራሉ ሕገ-መንግሥት ተፈፃሚነት

በዚህ ሕገ መንግሥት ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ሁሉ የፌዴራል ሕገ-መንግሥት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ነት ይኖራቸዋል። እንዲሁም በዚህ ሕገ-መንግሥት የተደነገጉት ድንጋጌዎች የፌዴራሉ ሕገ-መንግሥት ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረኑ ወይም የማይጣጣሙ ሲሆኑ የፌዴራሉ ሕገ-መንግሥት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

## አንቀጽ 41
## ሕገ-መንግሥት ማሻሻል

ይህን ሕገ መንግሥት ለማሻሻል የሚቻለው በሚከተለው አኳኋን ብቻ ይሆናል።

1. ሕገ መንግሥቱን የማሻሻያ ሃሳብ ከሁለቱ ጉባዔዎች ቢያንስ በአንዱ ሲነሳ፤
2. የማሻሻያ ሃሳቡ በሁሉም ጉባዔዎች ለየብቻቸው ውይይት ተደርጎበት ከእያንዳንዱ ጉባዔ በ2/3 ድምጽ ሲደገፍ እና
3. የክልሉ ምክር ቤት ማሻሻያውን በ2/3 ድምጽ ሲያፀድቅ ብቻ ነው።

## አንቀጽ 42
## ሕገ-መንግሥቱ የሚታተምባቸው ቋንቋዎች

ይህ ሕገ-መንግሥት በሐረሪ በኦሮምኛና በአማርኛ ቋንቋዎች ይታተማል። በሐረሪና በኦሮምኛ ቋንቋዎች መካከል የትርጉም ልዩነት ቢኖር የአማርኛው ቅጂ ተቀባይነት ይኖረዋል። እንዲሁም የሐረሪና የኦሮምኛ ቋንቋ በአንድ በኩል አንድ ዓይነት ሆነው ከአማርኛው ቅጂ ጋር የትርጉም ልዩነት ቢኖራቸው የሐረሪና የኦሮምኛ ቅጂ ተቀባይነት ይኖረዋል።